## ቅጥኝ [SYFILIS]

ቅጥኝ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ ሲሆን በሽታው በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ሳቢያ በፍትወተ-ሥጋ ብልቶች መካከል ወይም በፍትወተ-ሥጋ ብልትና በአፍ ወይም በፍንጥጣ ውስጥ ባለ ስስ ሽፋን መካከል ንክክ ሲኖር ነው። በሽታው በእርግዝና ጊዜ ከእናት ወደ ልጅ ሊተላለፍ ይችላል ፤ ደም በመስጠትም ይተላለፋል።

ኖርዌይ ውስጥ ቅጥኝ ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ከነጭራሹ ጠፍቶ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን እንደገና የተለመደ ሁኖአል። በኦስሎ ከተማ ውስጥ ከወንዶች ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በሚያደርጉ ወንዶች አካባቢ በሽታው ተዛምቶ ይታያል። በተጨማሪም በሽታው በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ጾታዎች መካከልም ይታያል። ቅጥኝ በቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረት አገሮች፤ በብዙዎቹ አዳጊ አገሮችና በተወሰኑ የሰሜን አሜሪካ ትላልቅ ከተማዎች ውስጥ የተለመደ ነው።

ኮንደምን በአግባቡ መጠቀም በበሽታው ከመያዝ ይከላከላል። የግብረ-ሥጋ ግንኙነቱ እስክፈጸም ድረስ ኮንዶሙ መውጣት የለበትም።

## ምልክቶች [Symptomer]

ቅጥኝ በሦስት ደረጃዎች ያድጋል።

ደረጃ 1፡

በሽታው ከተላለፈ በግምት በሦስት ሳምንቶች ጊዜ ውስጥ ባክቴሪያው ወደ ሰውነት የገባበት ቦታ ይቆስላል። ቁስሉ ብዙውን ጊዜ በብልቶች ላይ ይሆናል፤ ከዚያ ውጪም በፍንጥጣ፤ በአፍ ወይም የሰውነት ሌሎች ቦታዎች ሊሆን ይችላል። ቁስሉ ያን ያክል ሕመም የለውም፤ ከተወሰኑ ሳምንቶች በኋላም ያለ ሕክምና ራሱ ይጠፋል። ቁስሎች ባሉበት አካባቢ ዕጢዎች ያብጣሉ፤ ግን አያሙም። አልፎ አልፎ ይህ የበሽታው የመጀመሪያ ደረጃ ላይስተዋል ይችላል።

ደረጃ 2፡

በሽታው በመጀመሪያ ደረጃ ላይ ካልታከመ ከተወሰኑ ወራት በኋላ ወደ ደረጃ 2 ይተላለፋል። በዚህ ደረጃ ከሚከሰቱት ውስጥ እንደ በገላ ላይ የሚወጡ የተለያዩ የሽፌታ ዓይነቶች፤ የፀጉር መሰባበር፤ የዕጢዎች ማበጥ፤ ትንሽ የሰውነት ትኩሳት መጨመር፤ የራስ ምታትና የሰውነት መድከም ናቸው።

*ስውርነት*

በሽታው በደረጃ 2 ካልታከመ በሰው ላይ ምንም ዓይነት ሕመም ሳያሰማ ወደ አዲስ የስውርነት ደረጃ ይተላለፋል። በግብረ-ሥጋ ግንኙነት በሽታውን ማስተላለፍ ይቀንሳል፤ ግን በእርግዝና ጊዜ በሽታውን ወደ ፅንሱ ማስተላለፍ ይቻላል።

ደረጃ 3፡

ከብዙ ዓመታት በኋላ በሽታው ወደ ደረጃ 3 ይተላለፋል። በዚህም ደረጃ አንጎልን፤ ልብን፤ ቆዳንና አጥንትን ያጠቃል።

## ምርመራው [Undersøkelse]

ሐኪም ጋር በመሄድ ተራ የደም ምርመራ ተደርጎ ቅጥኝ እንዳለብህና እንደለለብህ ማረጋገጥ ይቻላል። በሌላ በኩል ግን በሽታው ከያዘ በኋላ ምርመራው አዎንታ [positive] ውጤት እስከ ሚያሳይ ድረስ የተወሰኑ ሳምንቶች ይወስዳል፡፤

## ህክምናው [Behandling]

የፐንሲሊን መርፌ ቅጥኝን ለማዳን መቶ በመቶ አስተማማኝ ነው። ለፐንሲሊን አለርጂ ለሆኑ ሰዎች ደግሞ ሌሎች ጥሩ ውጤት ያላቸው መድኃኒቶች ይገኛሉ።

ከበሽታው ነፃ መሆንህ ከመረጋገጡ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ማድረግ የለብህም።

**ነፃ ምርመራና ሕክምና** [Gratis undersøkelse og behandling]
**በተላላፊ በሽታዎች መከላከያ ሕግ መሠረት ቅጥኝ ለሕብረተሰቡ ሁሉ አደገኛ ተላላፊ በሽታ ተደርጎ ይተረጎማል፡፡ ይህም ማለት ማንም ለነፃ ምርመራና ሕክምና መብት አለው፡፡ አንድ ሰው በበሽታው ከተያዘ አሁን ላለው (ላላት) ወይም ቀደሞ ለነበረው (ለነበራት) የፍቅር ጓደኛ ማሳወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት አማካይነት በሽታው ወደ ሌላ ሰው መተላለፉን ለማረጋገጥና ለማከም እንዲቻል ሐኪሙና በሽተኛው በመተባበር በሽታው የተዛመተባችውን መስመሮች ይከታተላሉ፡፡**